## አሁንም ኳሱ በኛ እግር ስር ነች።

ማጋነን በሌለብት የምንመርጥ ከሆነ ኢትዮጵያዊ እስከሆንችና ተቃዋሚ ሆና ከወያኔ እስከተወዳደረች አህያም ብትሆን ምርጫችን እናደርጋታለን።

ለነገሩ ለአስራ ስምንት አመት በወያኔ/ኢህአዴግ ማልያ ህዝብን ወክላችሁ ለአንዴም ውሳኔያችሁ ላይ እግዚአብሔር የሰጣችሁን አይምሮ መጠቀም ከአልቻላችሁት መቶ በመቶ ትሻላላች። አህያ ጭነት ሲበዛባት ታለግማለች። የዛሬይቷ ኢትዮጵያ ላይ ሆኖ ነው እንጂ ወያኔ/ኢህአዴግ እንደድርጅት ለምርጫ እጩ ሆኖ መቅረብም አልነበረበትም ብለን እናምናለን። መስራች አባሎቻችሁ እንዳሉት የበሰበሰ ድርጅት ነው ያላችሁ።

## ድምጻችንን ለናንተ ሰጠን ማለት።

ኤርትራን ለማስገንጠል ለአስራ ሰባት አመት መዋጋታችሁ ትክክል ነበራችሁ ማለት ነው።

በአላስፈላጊው የኤርትራ ጦርነት በገፍ በደም የተከፈለው መሰዋትነት ሳያንስ የውንድሞቻችንን አሸናፊነት መና ማስቀረታችሁ ትክክል ነበር ደግ አደረጋችሁ ማለት ነው።

በጫካ አይምሮ በነደፋችሁት ፖሊሲ ምክንያት በረሀብ የረገፉት ዜጎች፤ አግባብ ያለው እውቀት እንዳያገኝ ያደረጋችሁት ትውልድ። ኢትዮጵያዊ የሆኑ በአለእውቀቶች እድሉን አግኝተው ፖሊሲውን ነድፈውት ቢሆን ለውጥ አያመጣም ነበር። የተሻለ ሌላ መንገድም አልነበረውም ማለታችን ሊሆን ነው።

ፍጹም ለአንድ ብሄር አድሏዊ የሆነው ዘረኛ ስረአታችሁ ተመችቶናል ማለት ነው።

የተለመደ ምርጫ ማጭበርበራችሁ። በይበልጥም በ97 ድምጻችንን አክብሩ ስላልን የገደላችኋቸው፤ ያጋዛችኋቸው፤ አሁንም በእስር የሚሰቃዩት ዜጎቻችን የሂወት ዋጋ ፍዳና መከራ አይሰማንም ማለት ነው።

መሬታችንን ለሱዳን ብትሰጡም፤ የመግዛት አቅሙ ለአለው ለገበያ አቅርባችሁ በትቸረችሩም ግድ የለንም። የሚቀር ካለ የቀረው ይበቃናል እያልን ነው ማለት ነው።

እናንተና የሰበሰባችኋቸው ዶንቆሮዎች የአሜሪካን ጦርነት ለመዋጋት ወንድሞቻችንን ሱማሌ ልካችሁ እሬሳቸውን ማስጎተታቸው እናንተን ስልጣን ላይ ስላቆየ እንደአክሽን ፊልም ተዝናንተንበት ምንም ሳይሰማን የምናልፈው ነው ማለት ነው።

በናንተ ዘረኛና ከፋፋይ ፖሊሲ በጅማ አንገታቸው በሰየፍ የተቀሉ፤ አርሲ እስከሂወታቸው ጉርጓድ የተጨመሩት፤ በወለጋ እርሻ ላይ እያሉ የተገደሉት፤

በቦረና በየጊዜው የሚገደለው ከፍተኛ ቁጥር ላለቸው ዜጎቻችን ምንም ተቆርቋሪነት የለንም ማለት ነው።

መለስን ጨምሮ ግብራበሮቹ በአለማቀፍ ፍርድ ቤት የሚከሰሱበት የጋንቤላ ወይ የኦጋዴን ዘር ማጥፋት በሰዎች ልጆች ላይ የተፈጸመ አጸያፊ ወንጀል። ጎሽ በርቱ የምንለው ነው ማለት ነው።

በዚህ ደረጃ ወርደን ለመገኘት ደግሞ በመጀመርያ ኢትዮጵያውያን ነን። ታሪካችንም ባህላችንም አስተዳደጋችንም አይፈቅድልንም።

የሰው ልጆች እንደመሆናችን ሂወት ለውሳኔ አስቸጋሪ የሆነ መንታ መንገድ ላይ ይወስደናል። በዚህ ጊዜ ምርጫ አድርገን የመረጥነው ውሳኔ ለውድቀታችንም ለስኬታችንም ወሳኝነት ነው።

ይህ በየግል ሂወታችን ነው።በተመሳሳይ ሁኔታ የአንድ አገር ህዝብ ለውሳኔ አስቸጋሪ የሆኑ ምርጫዎች ውስጥ በተለያየ ጊዜ እራሱን ያገኛል። በዚህ አይነት ጊዜ አብዛኛው ዜጋ የመረጠው መንገድ ለደህንነቱ ለሰላሙም እንዲሁም ለእድገቱ ወሳኝነት እንዳለው አሳምረን እናውቃለን።

ኢትዮጵያዊ እነደመሆናችን አስቸጋሪ የሆነ ውሳኔውኔያችንን የሚፈልግ ሁኔታ ከፊትለፍታችን አለ። ከጥቂት ወራት በኋላ አገራቀፋዊ ምርጫ ይካሄዳል። እንሳተፋለን አንሳተፍም። ከተሳተፈንስ ድምጹችንን ለማን ነው የምንሰጠው?። የመሳሰሉ ማስተዋልና ጥንቃቄ የሚፈልጉ ውሳኔዎች አይነት።

ድምጻችንን በመስጠት ምርጫው ልንሳተፍም ላንሳተፍም እንችላለን። ከተሳተፍንም አገር ቤት ያሉ ተቃዋሚዎች በሙሉ ምርጫው ላይ እንሳተፋለን ስላሉ። ድምጽ ለመስጠት መመዝገብ እንደተለመደው ከስራችንና ከትምህርታችን ጋር እየተገናኘ ስለሆነ ሞያ በልብ ብለን ልንመዘገብ እንችላለን። ምርጫው ላይ በጋራ ምንም ድርሻ አለማድረግ የሚለው አማራጭ ሁላችንን በአንድ የማያሰልፈን ከመሰለንም ልናደረገው እንችላለን። ሌሎችም ምክንያቶች ይኖሩናል።

መጪው ምርጫ እንደ አንድ አገር ህዝብ ለውሳኔ አስቸጋሪ እንደሆነ እናውቃለን። አስቸጋሪ ያደረጉት ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም። ከናንተ በኩል ያለው ግድያ እስር አፈና የድምጽ ዘረፋ የምንጠብቀው ነው። አዲስ ነገር የለውም። አስቸጋሪ የሚያደርግብን ምርጫው በተቃዋሚና በናንተ መካከል ብቻ የሚደረግ አለመሆኑ ። ተቃዋሚዎች መከፋፈላቸው እንዲሁም አንዳቸውም ጠንካራ ሆነው አለመውጣታቸው አይነት ምክንያቶች ናቸው። ለዚህ ወያኔዎች የሚወስዱት ድርሻ እንዳለ ተቃዋሚዎችም ከፍ ያለ ድርሻ እንዳላቸው እናውቃለን። ከባድ ችግር አድርገን ግን አናየውም። የሚቀርብልን በዚህ መንገድ ከሆነ እንደሌላችሁ ቆጥረን ውድድሩን በተቃዋሚዎች መሀል እናደርገዋለን። በግድ በድምጻችን እናስተባብራቸዋለን። እናንተን ለመታገል እስከሆነ ጥንካሬያቸውም ችግር የለውም፡፤ ከዚህ በፊትም ደካማ የነበሩትን በአጭር ጊዜ ጠንካራ አድርገን አሳይተናል።

በርግጥ ተቃዋሚዎች ለምራጭችን ተመችተው ቢሆን ተግባራችንን ያቀለዋል። ለአራተኛ ስልጣን ካልያዝን የምትሉት ከዚህ በፊት በተደረጉ ምርጫዎች ለምርጫችን አልገዛም ያላችሁት ናችሁ። ለዚህም ሌላውን ትተን በ97 የተደረገው ምርጫ ላይ በጉልበቱ ያላችሁበት ትልቁ እፍርታምነት በቂ ማረጋገጫችን ነው።

ሌላው በወያኔ ማልያ እንወክላችሁ የሚሉ ግለሰቦች ከዚህ በፊት በወያኔ ማልያ የህዝብ መወሰኛው ምክር ቤት ውስጥ ተዘፍዝፈው እያሉ ለአንዴም አልነበሩም። ሙሉ ውክልናቸውን ለአንድ ግለሰብ ለአስራ ስምንት አመት ሰተው የነበሩ ናቸው። እኛን አይደለም እራሳቸውን ለመወከል ጥንካሬው አንዳቸውም ለአንዴ እንኳ ኖሯቸው እንደማያውቅ እናውቃለን።

እራሳቸውን መወከል እንኳ የማይችሉ ሰዎች በመለስም ማልያ ይምጡ በልደቱ እነዚህ ላይ የምርጫ ውሳኔ ለመውሰድ ለሁላችንም ከባድ በአልሆነ። ሌሎቹን ሁሉ ምክንያቶች ትተን እነዝህ ሁለት ብቻ ምክንያቶች ወያኔ/ ኢህአዲግን ማላያ የሚመጡትን በሙሉ ከምርጫችን ውስጥ ለማውጣት ከበቂ በላይ አግባብነት ያላቸው ምክንያቶች ናቸው።

ምርጫው የሚካሄድ ከሆነ፤ ተቃዋሚዎች የሚካፈሉ ከሆነ። የያንዳንዳችን ደህንነትና ሰላም፤ በእኩል መብታችን ተከብሮ የአለአድሎ መኖር፤ ለቤተሰባችንም ለራሳችንም የሚያኖረን በቂ ገቢ ማግኘት። የልጆቻችን በቂ እውቀት አግኝቶ ማደግ። በይበልጥም የአገራችን ህልውና፤ የዜጎች በሰላም አብሮ መኖር እነዚህን የመሳሰሉ ተዘርዝረው ከማያልቁ ቁምነገሮች ጋር የምርጫ ውጤት ቀጥተኛ ግንኙነት እንዳለው እናውቃለን።

ተቃዋሚዎች ስለተከፋፈሉ። ተቃዋሚዎች ደካማ ስለሆኑ ወይ ስህተት ስለሰሩ። ውጤቱ ምንም ሆነ ምንም መለስ በጉልበቱ እቀጥላለው ስላለ። በፊት ጣት አሁን ደግሞ መዳፍ እቆርጣለው ብሎ ስለሚያስፈራራ። ከምር ሳናምንበት በቸልታ ወይ ምን ለውጥ ሊመጣ ብለን ችላ ብለን የምንተወው የማናደርገው ምንም ነገር አይኖርም። መኖርም የለበትም።

እነደአንድ አገር ህዝብ ሲጀመር ማንም ሀይል የፈለገውን ያህል ጉለበተኛ ነኝ ቢል የፈቀድነውን ለመምረጥም፤ ምርጫችንን እንዲያከበር ለማስገደድ ሀይሉ አለን። እስከዛሬም የጎደለን ይህን የህዝብ ሀይል በአግባቡ መስመር አሲይዞ የሚመራው ነው። ወደፊትም ማንም ይሁን ፍላጎታችንን አክብሮ ሀይላችን አስተባብሮ ለድል የሚያበቃን ካለ እሰየው ነው። ያም በአይሆን በግልም መታገል መብትን መጠየቅ የግድ መሆን ያለበት ነው። እያንዳንዳችን ድምጻችንን ለናንተ መንፈጋችንን ውጤቱ ምንም ይሁን ትግል አድርገን ነው የምናየው።

እስከዛሬ በመተባበርም በግልም ያደረግነው ትግል ትክክለኛም ተፈጥሯዊም ህጋዊም ነው።ድምጻችንን ልትመሩን የምትመጥኑን ስላልመሰለን የነፈግናችሁ በሙል። ምርጫችንን አክብር ስላልን መለስ ያስገደልካቸው፤ የተጋዙት፤ የተገረፉት፤ ስራቸውን ያጡት፤ በአለም ላይ ሁኔታዎች በፈቀደላቸው መንገድ ሲታገሉ

የነበሩትን በሙሉ። የአደረግነውን ትግል ትናንትም ዛሬም ነገም ስህተት ነበራችሁ የሚለን የለም። ትክክለኛ የሆነውን ማድረግ የነበረብንን ነው የአድርገነው።

ምርጫችን አልተከበረም ስንል መቶ በመቶ ትክክል ነበረን። ተሳስተንም ቢሆን ኖሮ ማንም ሀይል ከቻለ ሊያሳምነን ይጥራል። ይህን ማድረግ ከአቃታው ከፈለገ ከስልጣኑ ይለቀቅ እንጂ ሊገለን፤ሊያስረን፤ ከስራ ሊያባርረን፤ ሊያስርበን፤ በኩራዝ ሊያኖረን መብቱም ህጉም አይፈቅድም። የምናወራው በሚሊዮኖች ስለተጎዳንበት ነው።

ሲጀመር የማይገባንን አልጠየቅንም። ዛሬም እንደዛው የማይገባንን አንጠይቅም። ልትመሩን ብቃቱ የለቻሁም አናምናችሁም ነው የምንለው። መግደላችሁ ማሰራችሁ የውሸት ፕሮፓጋንዳችሁ የምንፈልገውን ከማወቀም ከመጠየቅም ከመታገልም አላቆመንም። ነገም አያቆመንም።

እስከዛሬም ጉልበተኞች ናችሁ ይሁን ብለን በቀላሉ የሰጠነው ነገር የለም። ነገም ቢሆን በሙሉ ሀይላችን ሳንታገል የምንሰጠው ወይ ይሁን ብለን የምንተወው ነገርም የለም። መጪው ምርጫ ላይም እንታገላችሁለን። እንደ97 ድምጻችንም በፍጹም አታገኙም። ዘርፋችሁ በስልጣን ለመቀጠልም አንገታችሁ ላይ ያገባነውን ሸንበቆ እንድታጠብቁት ማድረግያ ሳናስደርገው በቀላሉ እንደማይሆን እወቁት።

መጪው ምርጫ ላይ ስልጣናችሁን ለማስቀጠል የረዳል ብላችሁ ያወጣችሁትን እቅድ እናውቃለን። ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ ማስፈራራትና ተስፋ ለማስቆረጥ መሞከር ነው። ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው አሁን በሰፊው እየሰራችሁበት ያለው። ለምርጫው ያልተመዘገበ፤ ቆየት ብሎ ደግሞ እኛን ያለመረጠ ወደፍት ስራም አያገኝም ፤ መማርም አይችልም ብላችሁ የምትነዙት ባዶ ማስፈራርያ ነው። ይህን ማስፈራርያ ለአስራ ስምንት አመት አባባሉ ሳይቀየር ሰምተንዋል። የፈለገ ፈሪ ብንሆን ፍራቻችንን ደምጽ መስጫ ሳጆ ውስጥ ማናችንም ይዘነው ግን አንገባም እወቁት።

ሁለተኛው ተቃዋሚዎች ደካማ ናቸው፤ ተከፋፍለው ነው ያሉት። ፓርላማ ገብተው ለማሞቅ ነው። ምን ዋጋ አለው ድምጻችን መሰረቁ አይቀርም አይነት አባባሎችን ጣርያ አልፈው እስኪሰሙ ድረስ በሚያስገርም ሁኔታ እንደአዲስ ማስጮህ ነው።

እነዚህ አስተያየቶች በርግጥም እውነት ናቸው። እስካሁኑ በአለው ሰአት ተቆርቋሪ የሆነውም ዜጋ ድርጅቶችም ሲያነሷቸው የነበሩ መቆርቆሮች ናቸው። ችግሮቻችን ስለሆኑ የተሻለ ሆነን እንድንወጣ መነሳትም ነበረባቸው። ይህቺን ሰለምታውቁ ነው መራጩ፡ ተስፋ ቆርጦ ድምጹን ለኛ ይሰጣል ከሚል ተስፋ የእቅዳቸሁ አንዱ ክፍል አድረጋችሁ እንደአዲስ እነዚህን ነገሮች የምታጮሁት።

ከህዝብ ወገን ለሆንን ለሁሉም ጊዜ አለን። መቼ ተቃዋሚዎችን መተቸት መቼ ደግሞ አብሮነታችንን እገዛችንን ማሳየት እንዳለብን እናውቃለን። ይህም ብቻ አይደለም ሂደት ምን ደረጃ ድረስ መቃወም እንዳለብን አስተምሮናል።

ዋናው ጥያቄ ተቃዋሚዎች ስህተትን ስለሰሩ፤ስላልተባበሩ ድምጻችንን ለናንተ ለመስጠት በቂ ምክንያት አድርገን እንወስደዋለን ብላችሁ እንዴት አስባችሁት ነው። ከመነሻው ተቃዋሚዎች ላይ ያለን ቅዋሜ እናንተን ማሸነፍ በሚችል ጥንካሬ ወይ ለመምረጥ ለሁላችንም በማያምታታን ሀይላችንን በአሰባሰበ መንገድ  ለምን አልሆናችሁም ነው። ቅዋሜያችን ስታጮሁት ብትውሉ ከዚህ አይዘልም። ለማናችንም መዝለልም የለበትም።

በተመሳሳይ በ97 ምርጫ ድምጻችንን ስለዘረፋችሁና ድምጻችን ይከበር ስላልን ቅጣት ብላችሁ ስለገደላችሁን፤ ስላሰራችሁን፤ ስላስራባችሁን ፈርተን ድምጻችንን አንሰጣችሁም። በቀላሉ የሚሆን ነገር የለም ዛሬም መቀጠል ከፈለጋችሁ በጉልበት መስረቅ  ትችላላችሁ። ይህን ለማድረግም ደግሞ ከባለፈው የከበደ እንጂ ቀላል ሳንታገላችሁ ይሆናል ብላችሁ በፍጹም እናዳታስቡ።

አባባሏን ለየት በአለ አገላላጽ ከሌላ ምሁር የሰማናትም ቢሆንም መግቢያው ላይ በጠተቀምንባት አባባል  እንዘጋለን። እንደህዝብ ምን ብናድረግ ጥሩ ነው ለሚለው ይጠቅማል ያልነውን እንሞክራለን።

ምንም ማጋነን በሌለብት የምንመርጥ ከሆነ  ኢትዮጵያዊ እስከሆነችና ተቃዋሚ ሆና ከወያኔ እስከተወዳደረች አህያም ብትሆን ምርጫችን እናደርጋታለን። ለነገሩ ለአስራ ስምንት አመት በናንተ ማልያ ተወክለው ቀርበው ለአንዴም አይምሮቸውን መጠቀም ከአልፈቀዱት መቶ በመቶ ትሻላላች። አህያ ጭነት ሲበዛባት ታለግማለች፤ ዱላ ሲበዛባትም ልትራገጥ ትችላላች።

Saturday, January 30, 2010
Dakotareserch@yahoo.com